# መንግሥትና ፓርቲ አይደባለቁ!



10 Jun, 2017 በ ጋዜጣዉ ሪፓርተር

የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ትልቁ ፀጋ ትናንት ተቃዋሚ የነበረው ዛሬ ገዥ፣ ዛሬ ገዥ የሆነው ደግሞ ነገ ተቃዋሚ የሚሆንበት ነፃና ፍትሐዊ ዓውድ መፍጠሩ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ሥልጣን የያዘ ገዥ ፓርቲና መንግሥት በመካከላቸው በጉልህ የተሰመረ ድንበር ይኖራቸዋል፡፡ በእርግጥ ሥልጣን ላይ ያለ ፓርቲ ከሌሎች ሻል ያለ ተጠቃሚነት አለው ቢባል እንኳ፣ ገደቡ የተወሰነና በሕግ የሚመራ ነው፡፡ በመሆኑም የመንግሥትና የፓርቲ ሚና የመደበላለቅ ችግር አይታይበትም፡፡ ገደቡ ሲጣስና ገዥው ፓርቲ የአውራነት ባህሪ ተላብሶ ሁሉም የመንግሥት መዋቅሮች ውስጥ ገብቶ ሲያንጎዳጉድ ግን፣ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት አለ ለማለት አይቻልም፡፡ ማሰብም ይከብዳል፡፡ የመንግሥት ሹመቶች በሙሉ ፖለቲካዊ ሲሆኑና መዋቅሮቹ በካድሬዎች ሲሞሉ መንግሥትና ፓርቲን ለመለየት ያዳግታል፡፡ በዚህም ሳቢያ ስለዴሞክራሲ፣ ስለሰብዓዊ መብቶች፣ ስለፍትሐዊነትና ስለመሳሰሉት መነጋገር በፍፁም አይሞከርም፡፡ በኢትዮጵያ የአሁኑ ሁኔታ ይህንን ጉዳይ አንስቶ መነጋገር ያስፈልጋል፡፡ መንግሥትና ገዥው ፓርቲ እየተደበላለቁ ነውና፡፡

እንደሚታወቀው በአገሪቱ እስካሁን በተካሄዱ አምስት ብሔራዊ ምርጫዎች ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ ከአጋሮቹ ጋር በመሆን ፓርላማውን በበላይነት ተቆጣጥሮታል፡፡ አልፎ አልፎ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አነስተኛ የፓርላማ መቀመጫዎችን የሚያገኙባቸው አጋጣሚዎች የነበሩ ቢሆንም፣ ባለፉት ሁለት ምርጫዎች ነገሮች ተለውጠዋል፡፡ አንድም ተቃዋሚ ፓርቲ የሌለበት ፓርላማ ነው ያለን፡፡ ምንም እንኳ በቅርቡ ተቀስቅሶ በነበረው ሕዝባዊ አመፅ ምክንያት በምርጫ ሥርዓቱ ላይ ማሻሻያ ለማድረግ ቀጠሮ ቢያዝም፣ በአገሪቱ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት በሚፈለገው ደረጃ ካልሰፈነ የአንድ ፓርቲ የበላይነት መቀጠሉ አይቀርም፡፡ ይኼ ደግሞ ለዚህች አገር አስፈላጊ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔር ብሔረሰቦች፣ ቋንቋዎች፣ እምነቶች፣ ባህሎች፣ ወጎች፣ ልማዶችና የመሳሰሉት ያሉዋት አገር ናት፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ የተለያዩ ፖለቲካዊ አመለካከቶች የሚንፀባረቁባት አገር ናት፡፡ እነዚህ ፍላጎቶች ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መወከል አለባቸው፡፡ ይህ ውክልና የሚገኘው ደግሞ በእውነተኛ ዴሞክራሲያዊና ፍትሐዊ ምርጫ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ቀና መንገድ ላይ መጓዝ ሲቻል ከጠብና ከግጭት ይልቅ፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዕውን ይሆናል፡፡ በሕግ የበላይነት ሥር አገር የሚመራ ሥርዓት ይፈጠራል፡፡ የመንግሥትና የፓርቲ ሚናን መደበላለቅ አይቻልም፡፡

የመንግሥትና የፓርቲ ሚና እየተደበላለቀ የሚያስቸግረው ግን ለጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጀርባ በመስጠቱ ነው፡፡ በዚህም ሳቢያ በየቦታው የሚመደቡ የፖለቲካ ሹማምንት ግልጽነትና ተጠያቂነት ስለሌለባቸው ያሻቸውን ያደርጋሉ፡፡ ባለሙያዎች በተገቢው ቦታ ስለማይመደቡ የመንግሥት ተቋማት አሠራርና ብቃት ከደረጃው የወረደ ይሆናል፡፡ ሥራና ሠራተኛ ባለመገናኘታቸው የሠራተኞች ሞራል ስለሚነካ የሚፈለግባቸውን ኃላፊነት ከመወጣት ይልቅ፣ ምንቸገረኝነት ይበዛል፡፡ ግዴለሽነት ይስፋፋል፡፡ ሌብነት ልማድ ይሆናል፡፡ በዚህ ሳቢያ ሕዝብ ተቆጥቶ ጥያቄ ሲያቀርብ አዳማጭ ስለሌለ አመፅ ይቀሰቀሳል፡፡ ለንፁኃን ዕልቂትና ለንብረት ውድመት መዳረግ ይመጣል፡፡ ይህም የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ ግርግር በኋላ የተጠራቀሙ ችግሮችን ለመፍታት መውደቅና መነሳት ይጀመራል፡፡ ድርጊቶች ሁሉ በዕቅድና በጥናት ላይ ስለማይመሠረቱ ለተጨማሪ ስህተቶች በር ይከፈታል፡፡ እንደተለመደው ተግባር የማይጎበኘው የመፈክር ጋጋታ የዕለት ተዕለት ሥራ ይሆናል፡፡ በዚህ ምክንያት መንግሥትና ሕዝብ እንደገና ሆድና ጀርባ ይሆናሉ፡፡ መሬት ላይ የሚታየው ሌላ የሚሠራው ሌላ ይሆንና ወደተለመደው አዙሪት ይገባል፡፡ አገርን ችግር ውስጥ የሚከት አዙሪት፡፡

ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ ባለፉት 15 ዓመታት ያደረገውን ጉዞ ለመቃኘት መፍትሔ ለመፈለግ ‹ጥልቅ ተሃድሶ› መጀመሩን አብስሮ፣ ከላይ እስከ ታች መዋቅሩ ድረስ ግምገማ አካሂዷል፡፡ ይህ የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወግ በመሆኑ ምንም ችግር የለውም፡፡ አገሪቱን ላለፉት 26 ዓመታት እየገዛ ያለ ፓርቲ ችግር አለብኝ ብሎ ራሱን ሲገመግም ግን፣ የፓርቲና የመንግሥትን ዳር ድንበር ካላወቀ አሁንም መሠረታዊ ችግር አለ፡፡ የፓርቲው ተሃድሶ ከራሱ አልፎ መንግሥት መዋቅሮች ውስጥ በስፋት ገብቷል፡፡ ይህም አልበቃ ብሎ ሕዝብ ውስጥ በጥልቀት ደርሷል፡፡ ገዥው ፓርቲ የራሱን የውስጥ ችግር አንጥሮ ካወቀ በኋላ ለመንግሥት አመራሩና ለሕዝብ አስተዳደሩ የሚበጀውን ነገር ይዞ መምጣትና ተግባራዊ የመፍትሔ ዕርምጃ መውሰድ ሲገባው፣ የመንግሥት መዋቅሮችና ሕዝቡ ውስጥ ተሃድሶውን ይዞ መግባቱ ምን ይባላል? የመንግሥት ሠራተኞች በሙሉ አባሉ እንዳልሆኑ ይታወቃል፡፡ ሕዝቡም ቢሆን በአባልነት ሙሉ በሙሉ አልታቀፈም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ መቀላቀል ለመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ግንባታ መጨንገፍ አንዱ ምክንያት መሆኑን መረዳት በጣም ቀላል ነገር ነው፡፡ ይህ በፍጥነት መታረም አለበት፡፡ በአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነት ዴሞክራሲ ዕውን አይሆንም፡፡

በመንግሥት መዋቅሮች ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ የመጣው የግልጽነትና የተጠያቂነት መጥፋት ነው፡፡ በስንት መከራ የሚገኝ የመንግሥት በጀት በሕጉ መሠረት መጠቀምና ማወራረድ እያቃተ የአገር አንጡራ ሀብት እየባከነ ነው፡፡ የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ የሚታዩ አሳሳቢ ችግሮች የፓርቲና የመንግሥት መደበላለቅ የፈጠራቸው ችግሮች ናቸው፡፡ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ

የባለሙያና የካድሬ ዳር ድንበር በአግባቡ አለመሰመሩን፣ በኦዲትና በሪፖርት አቀራረብ ወቅት ከሚሰሙ ስሞታዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የመንግሥት በጀት ለታለመለት ዓላማ አልዋለም ሲባል ሕግ አልተከበረም ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ማናለብኝነት እንዳለ አስረግጦ ያሳያል፡፡ ይህ ችግር አፍጥጦ የሚታየው ደግሞ በተደጋጋሚ ስማቸው በሚጠራ መንግሥታዊ ተቋማት ውስጥ ነው፡፡ የዋና ኦዲተር፣ የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ የውስጥ ኦዲተር ሪፖርቶችና ሌሎች ጥናቶች ችግሩን ማረጋገጣቸው በተደጋጋሚ ሲነገር ነበር፡፡ ይህ ዓይነቱ ኃላፊነት የጎደለው ተግባር ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የማያስችል፣ በመንግሥትና በሕዝብ መካከል መተማመን እንዲጠፋ የሚያደርግና አገሪቱንም አደጋ ላይ የሚጥል ነው፡፡ ግልጽነትና ተጠያቂነት ሲጠፋ ውጤቱ አደገኛ ነው፡፡ የመንግሥትና የፓርቲ ሚና መደበላለቅ ከዚህ የከፋ አደጋም ያስከትላል፡፡

በሌላ በኩል ገዥው ፓርቲ ዛሬ ሥልጣን ላይ እንዳለ ሁሉ፣ ነገ ደግሞ ለሌላ ፓርቲ ሥልጣን በሕዝብ ምርጫ እንደሚያስተላልፍ ማሰብ አለበት፡ ፡ በሕገ መንግሥቱ ሥልጣን የሚያዘው በሕዝብ ይሁንታ እንደሆነ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ በተግባር የሚገለጸው ደግሞ ምርጫ ዴሞክራሲያዊና ነፃ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ፣ ሲቪክ ማኅበራት እንዲያብቡ፣ ሕዝቡ በነፃነት ሐሳቡን እንዲገልጽና የፈለገውን ፓርቲ እንዲደግፍ የሚያስችል የፖለቲካ ዓውድ እንዲፈጠር ማድረግ አለበት፡፡ ይህ ዘመን የአንድ ፓርቲ አውራነትን ለመቀበል የሚሻ ትውልድ የለውም፡፡ የአገሪቱ ብዝኃነት የሐሳብ ልዩነቶችንም በነፃነት ማስተናገድ አለበት፡፡ መንግሥታዊ መዋቅሮች ከፖለቲካ ፓርቲ ተፅዕኖ መላቀቅ አለባቸው፡፡  የአገር መከላከያ፣ ፖሊስና ሌሎችም የፀጥታ ኃይሎች የአገር አገልጋዮች እንጂ የአንድ ፓርቲ ወገንተኞች አለመሆናቸው በተግባር መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የሙያና ሕዝባዊ ማኅበራት በነፃነት ሊደራጁ ግድ ይላል፡፡ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚፈጠረው ኃላፊነታቸውንና ግዴታቸውን በሚገባ በተገነዘቡ ዜጎች ተሳትፎ ስለሆነ መንቃት፣ መደራጀትና ብሔራዊ ግዴታን በሕጉ መሠረት መወጣት መቼም የሚታለፍ አይሆንም፡፡ አገር ሰላም ሆና ሥልጡን ፖለቲካ ባህል የሚሆነው በዚህ መንገድ ብቻ ነው፡፡ በሕግ የበላይነት ሥር የምትተዳደር አገር መኖርዋ የሚጠቅመው አሁን ላለውም ሆነ ወደፊት ለሚመጣው ትውልድ ነው፡፡ የአገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ዜጎች በዚህ አገር ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲገነባ የበኩላቸውን ይወጡ፡፡ ጠብ፣ ግጭትና አላስፈላጊ ድርጊቶች አገርና ሕዝብ ስለሚጎዱ ማንም ተጠቃሚ አይሆንም፡፡ ለመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ዕውን መሆንና ለነገዋ ኢትዮጵያ ህልውና ሲባል ዴሞክራሲ የምር ይሁን፡፡ ለዚህ ደግሞ የመንግሥትና የፓርቲ ሚና በፍፁም መደበላለቅ የለበትም!

Source - http://ethiopianreporter.com/content